# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## የሌማት ቱርፋት በኃይል ማመንጫ ጣቢያ



ውድ አንባቢያን ! ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዕትሞቻችን የፕላኒንግ ዘርፍ የተቋሙን አጠቃላይ ሥራ በማቀድና አፈጻጸሙን በመከታተል ተቋሙን እንዴት በትክክለኛው ሀዲድ ላይ እየዘወረው እንዳለ አስነብበናችኋል:: ያልዳሰስናቸውን ሁለት ቀሪ የሥራ ክፍሎች ደግሞ በሌላው ዝግጅታችን የምናስቃኛችሁ ይሆናል:: ለዛሬ ግን ቀደም ሲል በተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተገለፁ ውጤታማ አፈጻጸሞችን በጣቢያዎች ተገኝተን ልናስቃኛችሁ ወድደናል:: ቅኝታችን ከአዲስ አበባ ከተማ ስለሚያስወጣን በምናብ አብራችሁን እንድትጓዙ ጋብዘናችኋል::

ዕለተ ሐሙስ መጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ከማለዳው አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ነው:: መነሻችን አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን መድረሻችን ደግሞ አዋሽ ቁጥር ሁለት እና ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫ እንዲሁም አዳማ ቁጥር ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ናቸው:: በዕለቱ የነበርን ተጓዦች እኔ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሙያተኞች ስንሆን ወደ ሥፍራው ለመሄድም ካለን ጉጉት የተነሳ ሁላችንም ከቀጠሮ ሰዓታችን አስቀድመን ተገናኝተናል::

ቼ! ፈረሱ እያለ የሚያስጋልበን ጥቁሩ መኪናችን ከተቀጣጠርንበት አራት ኪሎ በመነሳት ፊቱን ወደ ደቡብ ምሥራቅ አዙሮ የአዲስ አበባ ጎዳናዎችን እያቆራረጠ የአዲስ አበባ - አዳማን ፈጣን መንገድን ተያይዞታል:: ዐይናችን በመንገዱ ግራና ቀኝ ያለውን ድባብ እያስቃኘን፣ እኛም ተጓዦቹ ስለመንገዳችን እያወጋን፣ ጥቂት እንደተጓዝን፣ ከምኔው በሚያስብል ግርምት ከምሥራቅ ሸዋዋ አዳማ ከተማ ገባን:: እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ የከተማ ነዋሪዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ከኤሌክትሪክ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ ጎህ ከመቅደዱ የከተማዋ ሆቴሎች፣ ጸጉር ቤቶች፣ ሻይቤቶች፣ ባንክ ቤቶች፣ ወዘተ ሀሳባቸውን ኤሌክትሪክ ላይ ጥለው ሥራቸውን መከወን ጀምረዋል:: ኤሌክትሪክ የከተሞችን ጭጋግ ገላልጦ ዐይኖቻቸውን ስለሚያበራላቸው የአዳማ ከተማም በፈገግታ ፈክታና ደምቃ ትታያለች::

የቀድሞው የኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ባለስልጣን የአሁኑ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የበኩር ልጅ የሚባለውንና ከአዲስ አበባ ከተማ በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኘውን የአባ ሳሙኤልን የውኃ ኃይል ማመንጫ ተከትለው በሁለተኛ፣ በሦስተኛ እና በአራተኛ ደረጃ እንደቅደም ተከተላቸው የተወለዱት አዋሽ አንድ (ቆቃ) አዋሽ ሁለት እና አዋሽ ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ናቸው:: እነዚህ ጣቢያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ገና የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ባልተስፋፋበት ወቅት የተፈጠሩ በመሆናቸው ለአገራችን ብርቅ ክስተቶች ነበሩ:: ዛሬም ድረስ እያበረከቱ ባሉት አስተዋጽኦ ይሞገሳሉ፤ ይወደሳሉ፤ በአንጋፋነታቸውም ይከበራሉ::

አሁንም ጉዞ ላይ እንዳለን አትርሱ:: የአዳማ ከተማን የተሽከርካሪዎች እና የሰዎች ትርምስ አልፈን ወደ መዳረሻችን በሚወስደን መንገድ ላይ እየተመዝገዘግን ከመቅጽበት አዋሽ ቁጥር ሁለት እና ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በር ላይ ደርሰናል:: ከከፍተኛ የማሽከርከር ጥንቃቄ ጋር የካፒቴናችን የምድር በረራ እና የመኪናችን ፍጥነት አጃኢብ ነው!

ልብ በሉ አመጣጣችን በዋናነት በኃይል ማመንጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ ስለሚከናወኑት የጥገና ሥራዎች እና የጣቢያዎቹን አጠቃላይ ቁመና ለማስቃኘት ያለመ ቢሆንም ከግቢው መግቢያ ጀምሮ በአረንጓዴ ልማት የተሸፈነው የልማት ሥራ ቀልባችንን ሰቅዞ ስለያዘን የፕሮግራማችን አንዱ አካል አድርገነው ሳንወድ በግድ ሽፋን ልንሰጠው ወደድን::

ገና ወደ ግቢው ሲዘለቅ በተፈጥሮ ዛፎች፣ በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ተውቦ የምናገኘው አረንጓዴ ስፍራ ለዓይን ማራኪነቱ አጀብ ያስብላል:: በተለይ ከመግቢያው በስተቀኝ በኩል ያለው ሰፊ ቦታ በፓፓዬ ተክሎች ተሸፍኗል:: ትንሽ እልፍ እንደተባለ ግራ-ቀኙን የተንጣለለው የእርሻ መሬት በቆስጣ፣ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ሰላጣ፣ ሽንኩርትና በመሳሰሉት የጓሮ አትክልቶች ተሸፍኗል:: ይህን አረንጓዴ ልማት ድንገት ሲመለከቱት የግብርና ተሞክሮ የሚካሄድበት አንድ ትልቅ የምርምር ማዕከል እንጂ ሌላ ተልዕኮ የሚካሄድበት ሥፍራ አይመስልም::

የአዋሽ ሁለትና ሦስት ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ተወካይ ኃላፊ እና የጥገና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ሮቤል አበበ እንደሚገልጹት፤ የመሬትና ውሃ ሀብት መኖሩን ተከትሎ የጣቢያው ሠራተኞች በግቢ ያሉ ቦታዎችን በትርፍ ጊዜያቸው እያለሙ መጠቀም ከጀመሩ ረዥም ዓመታትን አስቆጥረዋል:: ይህም የልማት ተግባር በጣቢያው ሠራተኞች የመረዳጃ ዕድር የሚመራ ነው::

በኃይል ማመንጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ የሚኖሩ ሠራተኞች አትክልት ለመግዛት ገበያ አይሄዱም ይላሉ ኢንጂነር ሮቤል፤ ከፍጆታ የሚተርፉ ምርቶችን እንዲሁም ችግኞችን በማፍላት ለአካባቢው ማህበረሰብ በአነስተኛ ዋጋ እየሸጡ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውንም እየተወጡ ይገኛሉ:: የቀን ሥራ እየሠሩ የሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪዎችም በግቢው ውስጥ ከሚሠራው የአረንጓዴ ልማት ጋር ተያይዞ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆኑን አጫውተውናል::

ለዐይን ማራኪ ሆኖ የሚታየው ይህ የአትክልት ቦታ ቀደም ሲል በተለያዩ እሾሃማ ተክሎችና ሳሮች እንዲሁም አለቶች የተሸፈነ ነበር ያሉት ኢንጂነሩ፤ ሠራተኛው ባለው ትርፍ ጊዜ እራሱ እየቆፈረ፣ እየተከለ እና እየተንከባከበ ያለማው ልማት ከዐይን ማራኪነትና መናፈሻነት በተጨማሪ የኢኮኖሚ ምንጭ ሊሆናቸው ችሏል:: ከሽያጭ የሚያገኙትን ገንዘብም ደግሞ ለአንዳንድ ማህበራዊ ጉዳዮች ያውሉታል:: አሁን ያለውን ልማት በመጠንም ሆነ በዓይነት ለማስፋት በቀጣይም ሸንኮራ አገዳ እና ጌሾን የመሳሰሉ አትክልቶችን ለማልማት ቦታዎች ተዘጋጅተዋል:: ይህ በጎ ተግባር በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረውን የጓሮ አትክልት ልማት የሚደግፍና የሚያስፋፋ ነው:: በዚህ መልካም ተሞክሮም ከአካባቢው መስተዳድር ምስጋና እንዳቀረበላቸው ኢንጂነሩ ገልጸዋል::

ለዛሬ በዚሁ እናብቃ:: በቀጣይ ሳምንት ወደ አሳደርነው ጉዳይ ተመልሰን የአዋሽ ሁለት እና ሦስት የውኃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችን አመሠራረትና አሁን ያሉበት ቁመና እናስነብባችኋለን:: እስከዚያው ቸር እንሰንብት::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ